# የቴዲ ጉዳይ ጥንስስ

ወልደሚካኤል መሸሻ * - 14 September 2008

ቀደም ሲል “አሁንም ፍትህ ለይቅርታ?” በሚልና “ቴዲ አሁንስ አልቀረለትም” በሚል ርዕስ የወጣቱን አርቲስት ወንጀል ጉዳይና የፍርድ ቤቱን አካሄድ በማስመልከት ዘገባዎችን አቅርቤአለሁ። ከጅምሩ ከውንጀላው አመጣጥ ጋር በማያያዝ በቴዲ ላይ ምን እንደታሰበ፣ የፍርዱ ዳኛ የዳኝነት ተግባር ሳይሆን፣ እያደረጉ ያሉት የዐቃቤ ሕግን ጭምር መሆኑን ለማስገንዘብ ምክሬአለሁ። በመጨረሻ የሆነውም እንደተነበይኩት ዓይነት ይመስለኛል። ልዑል አይኑን ጨፍኖ ተከላከል ሲል በየነ። ዳኝነትንና ዳኛን አንገት የሚያስደፋ ብይን። ያ ቀን አይመጣ መስሎት፤ ያ ቀን አይደርስ መሎት። ለርሱና ለቤተሰቦቹ፣ ለዘሮቹ ይብላኝላቸው እንጂ ቴዲ እንደ ሆነ ያ ቴዲ ነው። አይሟም፤ የበለጠ ይጠነክራል እንጂ አንገቱን አይደፋም። ቆራጥ የኢትዮጵያ ልጅ ነውና። ወድ ወገኖች ፍ/ቤቱ ቴዲ የመከላከያ ማስረጃዎችን እንዲያቀርብ ለመስከረም 27 ቀን 2001 ዓ.ም መቅጠሩ ይታወሳል። ከቶውንም በማንኛውም መልክ ቴዲ ተመስክሮበታል የተባለበትን ጭብጥ ቢያስረዳም፣ ሁለት ሃላፊነት ይዞ ከቀረበ ዳኛ ፍትህ ይገኛል ብሎ መጠበቅ ጠብ ይልልኛል ብላ በሬን ስትከተል ቆይታ መና እንደቀረችው ዓነት ቀበሮ መሆን ይመስለኛል። አገረ መንገዴን እንዲህ ለትውስታ ያህል የፍትህ አካሄዱን  አነሳሁ እንጂ አነሳሴ ቴዲ ላይ የቀረበበት የፈጠራ ወንጀል የአመጣጡ ጥንስስ እንዴት እንደነበር ለማሳየት ነው።

“የትግራይ ህዝብና የትምክህተኞች ሴራ ከትናንት እስከ ዛሬ” በሚል መምህር ገብረኪዳን ደስታ የተበለ አንድ የተረገመ ወያኔ በ1998 ዓ.ም ያሳተመውን መጽሐፍ አንድ በቅርብ ከአገር ቤት የመጣ ሰው እየው እስኪ ብሎ ሰጠኝ። መጽሐፉን ገለጥ አድርጌ ስመለከተው፣ በእጅጉ አስደንጋጭ ነው። ታዲያም የመጽሐፉ ይዘት በአጭሩ ጠቅለል ተብሎ ሲታይ፣ በአንድ በኩል ከጥንት ጀምሮ የትግራይ ሕዝብ ከማናቸውም የኢትዮጵያ ሕዝብ የበለጠ ጀግና እንደነበር ለማሳየት የተሞከረበት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ምንኛ ሌሎችን የኢትዮጵያ ማህበረሰቦችን ዝቅ አድርጎ  ለማየት የተሞከረበትና ራሱ ወያኔ ኢሳያስን ከሥልጣን አስወግዶ ከትግራይ ጋር ቀላቅሎ ጥንት ሲጀምር ወዳለመው የትግራይ-ትግሪኝ መንግሥት ለመመሥረትና ለማወጅ መንገድ እየጠረገ መሆኑንና ያንን ድብቅ ዓላማቸውን ቁልጭ አድርጎ ያመላከተ ሆኖ አገኘሁት። መጽሐፉ እንደተለመደው ከትግራይ ብሔረሰብ ውጭ የሆኑትን ከምኒልክ ጀምሮ ያሉትን መሪዎች፣ ዕውቅ ጸሐፊያን፣ ዕውቅ ምሁራንን በተለይ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያምን ጨምሮ የሚኮንን፣ የሚያወግዝና የሚያብጠለጥል ነው። ፍጹም የዘረኝነትን መርዝ የተረጨበት የሚያሳይ መጽሐፍ ነው።

መጽሐፉ ልክ አፄ ምኒልክ ከጉድጓድ ወጥተው በትግራይ ሕዝብ ላይ እንዳፈጠጡ ዓይነት ያስቀምጣቸዋል። እስኪ ከመጽሐፉ ውስጥ፣ “… የትግራይ ሕዝብ ሞት፣ የትግራይ ሕዝብ ውድመት፣ የትግራይ ሕዝብ እልቂት ወዘተ ለአፄ ምኒልክ የመንፈስ እርካታ ነው የሚሰጣቸው። ምክንያቱም የአፄ ምኒልክ ዋና ዓላማ የትግራይን ሕዝብ ማደህየት፣ ማዳከምና መበታተን ነውና።” የሚለውን አባባል እንመልከት። አባባሉ አፄ ምኒልክን ለመኮነን የተደረገ አነሳስ ይሁን እንጂ፣ ያው ወትሮም እንደሚቀሰቅሱት፣ ትግራይም ወደ ኢትዮጵያ የተቀላቀለችው በአፄ ምኒልክ በሃይል ርምጃ ነው ለማለት ነው በአጭሩ። በመሠረቱ አፄ ምኒልክ የነበሩበት ዘመን በሁሉም ዓለም ክፍሎች ግዛት እያስፋፉ አንድ አገር ማድረግ ነው። ከርሳቸው በፊት የኢትዮጵያ መሪ አፄ ዮሓንስ

የጀመሩትን ነው ምኒልክ የተከተሉት። በኤውሮፓ፣ በእስያ፣ በአፍሪካ ሁሉ ተፈጽሞአል። የቀናው ወደፊት ይገፋል፤ ያልቀናው ደግሞ ገብሮ ወደ ውህደት ውስጥ ይገባል።

በኤውርፓ የተደረጉት የአንደኛውና የሁለተኛ የአለም ጦርነቶች አነሳሳቸው በዚህ መልክ ነው። ኤውሮፓ ከዩጎዝላቪያ፣ ከሶቪዬት ሕብረትና ቼኮዝላቢያ አሁን በቅርብ ከመበታተናቸው በፊት አብዘኛው የኤውሮፓ አገሮች የጸና የግዛት ቅርጽ የተገኘው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ነው። የኢትዮጵያ ግዛት የተዋቀረው ደግሞ ከነዚህ ሁሉ ቀደም ብሎ ነው። ለምሳሌ ያህል ጀርመን በብስማርክ ወቅት የተወሰኑ የጎረቤት አገሮችን በኃይል ይዛ ነው። በኤውሮፓ ከአነስተኛ አገሮች አንዷ የሆነችው፣ ቤልጅየም የተመሰረተችው ከጦርነቱ በኋላ ከሰሜን ኔዘርላንድስ እና ከሰሜን ፈረንሳይ የተወሰነውን ክፍል ይዛ ነው። በሌላ በኩልም ፊንላንድና ፖላንድ ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በፊት የራሽያ ፌዴሬሽን አካል ነበረች። የአሁኗ ቱርክ ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በፊት ኦቶማን ኢምፓየር ሲባል በነበረበት ወቅት ግዛቷ ኢጅግ ሰፊ እንደነበር ይታወቃል። የአሁኗን ቅርጽ ያገኘችው ተሸንፋ ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ነው። የኢትዮጵያ ግዛትም ቀደም ብሎ እስከ የመን ድረስ እንደሆነ ይነገራል። ታዲያ እንዲ ሆኖ እያለ በኣፄ ምኒልክ ሬሳ ላይ የሚወረድበት የዘረኝነት ቅስቀሳ እልቂትን ለመጋበዝ ካልሆነ በስተቀር፣ ምን ለማምጣት እንደሆነ የሚገመትም አይሆንም። እንዲህ፣ እንዲህ እያዘጋጁና እያነሳሱ ሕዝቡን ሌላውን ኢንተርሃሞይ ይላሉ፤ ዘረኛ ይላሉ። የእምዬን ለአብዬ።

ሌላው በዚህ መጽሐፍ የተያዘው ትልቁ ቦታ በፕሮፌሰር መስፍና ላይ የሚደረገው በዘረንነት ስም ውግዘት ነው። ለግንዛቤ ያህል፣ በመጽሐፉ ገጽ 163 ላይ፣ "....አንድ ሰው ክርስትና ሲነሳ አማራ ሆነ ይባላል በማለት ነው ያለ ሐፍረት የሚናገሩት። በሌላ አነጋገር እስላም ብሎ አማራ የለም የሚል እምነት ነው ያላቸው።" ይላል እርሳቸው አማራ ብሎ ብሔር የለም ላሉት። ምን ከምን ለማገናኘት እንደተፈለገ ፍርዱን ለናንተ።

ደግሞም ሌላ፣ "የህወሓት ታጋዮች ለትምህርትና ለእውቀት ባዕድ ናቸው። ትምህርትን ጠልተው ጫካ የገቡ ልጆች ነበሩ እያሉን ነው። <u>የፕሮፌሰሩ አስተሳሰብ ከዶሮ ላባ የቀለለ ተራ ነገር ቢሆንም፣ አባባላቸው  የህወሓት ታጋዮችን ብቻ የሚመለከት ነው ብሎ ማሰብ አይቻልም።"</u> በሚል አነጋገር የፕሮፌሰርን ከትግራይ ሕዝብ አልፈው ከሌሎችም የኢትዮጵጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ለማጋጨት የተደረገ ሙከራ። ብቻ ስንቱ እንዳይሞቱ እንዳይድኑ አድርጎ፣ ከቆጡና ባጡ አምጥቶ ድራሻቸውን ለማጥፋት መንገድ የሚጠርግ ጽሁፍ ነው። እኔ ውጭ ስለሆንሁ አሁን አገኘሁ እንጂ፣ ፕሮፌሰር አገር ውስጥ ስለሆኑ በእጅጉ አስከፊ የሆነውን የስም ማጥፋት ውንጅላ መጽሐፉን አግኝተው ሳያነቡት ወይም ይህን የተነገረባቸውን ሳይሰሙት እንደማይቀሩ እገምታለሁ። በዚህ በኩል በእንዲህ የተነገረባቸውን አስቀሚና ያለሥራቸው የተደረተባቸውን የስም ማጥፋት ውንጀላን፣ እንዲህ የውርደት ካባ ያለሥራቸው መከናነባቸውን እያውቁ ዝም ብለው ከሆነ፣ ለምን? ያውም ዘረኛን መሠረት ባደረገ ጭፍጨፋ። ዘረኝነት ደግሞ አስቀያሚና አሰቃቂ የሆነ የወንጀሎች ወንጀል ነው። ለምን ግን ፕሮፌሰር? አምነው ወይስ ፈርተው? ወይስ የትግል ስልት ብለው? ወይንስ እኔን እንደፈለጉ ያድርጉኝ ነው? ወይንስ እስሩን አንዴ አቅምሰውኛልና ከእንግዲህ ምንም አይሉኝም ነው? እነዚህንና የመሳሰሉትን መላምታዊ ምክንያቶችን መደርደር ይቻላል። እኔ መጽሐፉን ያነበብሁት ሰውነቴን እየወረረኝ ነበር። ፕሮፌሰር እንዲህ ከትውልድ ትውልድ በሚተላለፍ መልኩ ተጽፎባቸው ምን አሉ? መቼም ምንም ነገር የሚጀመርው ከራስ ነውና። ይህን አልፈው ከሆነ ለምንድነው ፕሮፌሰር መስፍን አሁን፣ አሁን በትጥቅ ትግል ላይ የትናንትን እያነሱ ዘመቻ የጀመሩት? እውነት ወያኔ በየቀኑ ደም አፍሶ ስለመምጣቱና ሥልጣን ስለመያዙ

እየዘመረልን በሰላም ሥልጣን ይለቃል ብለው ይሆን? ነገሩ ቢሆን ቀና አስተሳሰብ ነው። ግን እስከዛሬዋ ድረስ ካየነው ባሕርይው አይመስለኝም። እናም፣ ፕሮፌሰር መስፍን ለዚያች አገር እድሜ ልካቸው ጮኸውላታል፣ ታግለውላታ፣ ግን አሁን፣ አሁን በዚህ በመጨረሻ ዕድሚያቸው የእንዲህ ተቃውሟቸው ወዲህ ወዲያ ብለው አልገባ ይለኛል። ምንም እንኳ ጦርነት አስቃቂና መጥፎ ቢሆንም፣ ምናለ ምርጫውን ለመራጩ ቢተውት?

ለነገሩ መጽሐፉ ሁሉን የኢትዮጵያ ቁርጥ ቀን ልጆችን ለግብዓተ መሬት ስሏቸዋል። በምርጫ 97 ለየፓርትዎቻቸው ከፍተኛውን የቅስቀሳ ተግባር ሲፈጽሙ የነበሩት የሕብረቱ አክሊሉ ዘለቀ፣ የቅንጅቱ ደበበ እሸቱም ከዘረኝነት ጎራ ውስጥ ተወርውረዋል። <u>ከሁሉ እኔን የገረመኝ ግን ያ በግምት ስንለው የነበረው የቴዲ ጉዳይ ጥንስሱ ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ መገኘቱ ነው።</u> እናም፣ የቴዲን ሳምንት ምክንያት በማድረግ ሁኔታውን ላስጨብጣችሁ ወደድሁ። ቀጥለን እንይ።

እመጽሐፉ ገጽ 239 ላይ፣ "ቴዲ አፍሮ የተባለው አርቲስትም እንዲሁ፣

የትምክህተኞችንና የዘረኞችን ዓላማ ለማሳካት ነበር" በማለት፦

> "በአሥራ ሰባት መርፌ በጠቀመው ቁምጣ ፣
> ለለውጥ ያጎፈረው ዙፋን ላይ ሲወጣ፣
> እንዳምናው ባለቀን የአምናውን ከቀጣ፣

አዲስ ንጉስ እንጂ ለውጥ መቼ መጣ የሚሉ ስንኞች የሚገኙበት ካሴቱን በግንቦቱ ምርጫ ዋዜማ የለቀቀው።" ይላልም ጸሀፊው ስንኞቹን ሲተች፣ "ቴዲ አፍሮ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች አሥራ ሰባት ዓመት ሙሉ እምቢ ለጭቆና ብለው የሞት የሽረት ትግል በማካሄድ የከፈሉትን ክቡር የመስዋዕትነትና የተጎናጸፉትን ብሔራዊና ሃገራዊ መብትን ነው ትርጉም የለሽ ነው እያለን ያለው። ለኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች መብትና ሕልውና ሲሉ የሕይወት መስዋዕትነት በከፈሉት ጀግኖችና ሕዝቦች ላይም ከመሳለቅ አልተቆጠበም። ደማቸው ደመከልብ እያለን ነው።" ብሎ ይደመድማል። ከያስተስርያል ዜማው የተወሰደ መሆኑ ነው። ይህ መጽሐፍና ይህ የተነገረበት ውንጀላ ምንኛ ወያኔ በቴዲ ላይ ቂም እንዳበቀለበት ያለጥርጥር ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል ብዬ እገምታለሁ። እናም፣ እስኪ በአጭሩ ፈታ አድርገን የጸሐፊውን ቀስቃሽ አነጋገሩን አንድባንድ እንመልከት።

**ትምክህተኛነት፦** ቴዲ አፍሮ የተባለው አርቲስትም......የትምክህተኞችንና የዘረኞችን ዓላማ ለማካሳት ነበር ብሎ ነው የተነሳው። ቴዲን ትምክህተኛና ዘረኛ አድርጎ በደመደመ ሁኔታ። ነገሩ የእምዬን ለአብዬ ዓይነት ነው ሁሌ የወያኔ ሥራ። እስኪ የዚህ ዜማ ስንኝ ምኑ ላይ ነው የቴዎድሮስን ትምክህተኛነትን የሚያሳየው የትምክህት ትርጉሙ ጸሐፊው ካልገባው በስተቀር። አድቫንስድ ለርነርስ በተባለው የእንግሊዝኛ መዝገበ-ቃላት ላይ፣ ትምክህት (chauvinism) ከመጠን ያለፈ የአርበኝነት ስሜት( excessive patriotism)፣ አንደኛው ወገን በሌላው ላይ የበላይነት እንዳለው አድርጎ ማመን(prejudiced belief of superiority by one group over another) ይልና በምሳሌነትም የወንድ ትምክህት(male chauvinism) በማለት ያስቀምጣል። ከኛ በላይ ተዋጊ የለም፣ ከኛ በላይ ጀግና የለም፣ እኛ የደም ዋጋ የከፈልንበትን የመንግሥት አስተዳደር ማነው የሚወስድብን? እያሉ ሌት ተቀን ሲፎክሩ ያየናቸውና የምናያቸው። ታዲያም ይኸው አካሄድ አይደለም እንዴ ትምክህተኝነትን የሚያሳየው? ይኸው አካሄድ አይደለም ወይ የበላይነትን የሚያሳየው? ታዲያም ከዚሁ ተነስተን ጸሐፊው ከጌቶቹ

በተነገረው መሠረት በቴዲ ላይ የለጠፈውን ውንጀላ ስንመዝን የተገላቢጦሽ አይሆንባችሁም ወገኖቼ?

ቴዲ በዚህ ዘፈን የስንኝ ቋጠሮው ለወያኔ በትክክል ለመንገርና ለማስተላለፍ የፈለገው ወይም ያስተላለፈው፣ የመጣችሁበት ሌላ፣ የምትሰሩት ሌላ። ለኢትዮጵያ መሻሻልና ለውጥ አመጣለው ብሎ ንጉሱን ገልብጦ ሥልጣን የያዘው መንግሥት(ደርግ) በበቀልኝነት እነዚያን ባለሥልጣናትንና እነዚያን ወጣቶችን፣ አዛውንትን በጠቅላላው ሕዝብን ጨረሰ። እናንተም(ወያኔ-ኢህአዴግ) ሥልጣን ስትይዙ ለኢትዮጵያ አገራችን ለውጥ እናመጣለን፣ ዲሞክራሲን እናሰፍናለን ብላችሁ ለውጥ ሳይሆን፣ በብቀላ ጀመራችሁ፤ የያለፈውን መንግሥትን ፈለግ ተከተላችሁ፣ ያለፈውን መንግሥት ስህተት ፈጸማችሁ። አልፋችሁ ተርፋችሁ ሕዝቡን በዘር ከፋፍላችሁ አበጣበጣችሁ፣ አተረማመሳችሁ፣ ኢትዮጵያዊነትን እያጠፋችሁ ናችሁ፣ ተግባራችሁ መግደል፤ ማሰር፣ መደብደብ፣ ማባረር፣ ማፍረስ ሆነ። እናም፣ በዘር አትከፋፍሉን፣ ቂምበቀልነት ይቁም፣ ተውትና ወደ አንድነት መልሱን ይቅር ተባብላችሁ እያለ ነው። ታዲያ እምኑ ስንኝ ላይ ነው የትምክህት ባሕርይ የሚታየው? ሾላ በድፍኑ ይሏል እንዲህ ነው። ለነገሩማ ያለመታደል ሆኖ ነው እንጂ፣ እንዲህ ዓይነት ሂስ አዘል ሙዚቃዎች ላወቀበት መንግሥት ወይም ባለሥልጣን ራሱን ማሳያ መስተዋት ናቸው ሕግ ባለበት አገር። ሕግ በተደመሰሰበት አገር ሆነና ቂም አስይዞ በትምክህት፣ በማን አለብኝነት ለእንደምናየው ዓይነት ንጹህና ወጣቱን ለሰለባ ዳርጎታል።

ዘረኛነት፡- በአጠቃላይ ዜማው የዘረኝነት ትልምንም ለማሳካት ነው ይላሉ ጸሐፊው። ወደ አባባሉ ሳንሻገር ዘረኝነት ምን ማለት እንደሆነ ግንዛቤ ቢኖረን፣ ዘረኝነት(racisim) ይላል አድቫንስድ ለርነርስ መዝገበ ቃላት፣ አንዱ ዘር በሌላው ላይ የበላይነት አለው ብሎ ማመን። a belief in the superiority of one race over another. እስኪ ያው ሾላ በድፍኑ ካልሆነ በስተቀር የትኛው ስንኝ ላይ ነው በእንደዚህ የሚታየው። ይልቁንም ለእውነት፣ ስለእውነት ከተባለ ዘረኛ ማነው? ከዚህ ከጀግና ህዝብ መወለዴ ያኮረኛል ብሎ አንድን ብሔር አግዝፎ የተናገረ መሪ በኢትዮጵያ ውስጥ ማነው? ቴዲ እኮ በአንጻሩ እያለ ያለው ሁሉም ተቻችሎ፣ እርቅ ተፈጥሮ ወደ ነበርንበት ወደ አንድነታችን እንመለስ ነው። አንዳችም ለዘርኝነት ትርጉም የሚያሻግር ስንኝ የለውም። መቼም ሊበሏት ያሰቧትን ወፍ ጅግራ ይሏታል ዓይነት ነው ነገሩ። ወያኔ መቼውንም ቢሆን ስለአንድነት ሲነሳ፣ ስለእርቅ ሲነሳ ያመዋል። እርቅ ሲባል ከማን ጋር ተጣላን ይላሉ። አይናችሁን ጨፍኑ፣ ልባችሁን ሰውሩት ዓይነት ነገር። እነርሱ ዓይን የላቸውም እንጂ፣ እነርሱ ጆሮ የላቸውም እንጂ፣ እነርሱ ሕሊና የላቸውም እንጂ ምርጫ 97 በግንቦት 7 አሳይቷቸው፣ ነግሯቸው ነበር። ያዶቀሰ ሰይጣን… ምን ሳያደርግ አይለቅም ዓይነት ሆነና ለሥልጣን ማቆያ ጉቦ መሬት መስጠት ላይ ተደርሶአል።

ገና ምርጫ 97 ቅስቀሳ ሲጀመር ወያኔ-ኢህአዴግ የኢንተርሐሞይን የዘረኝነት ጦር ማናፈስ የጀመረው ራሱ ነው። ይህን የኢንተርሐሞይን መፈከር ከዶ/ር ነገደ ጎበዜ መጽሐፍ ጋር እያጣቀሰ በየምርጫው ቅስቀሳ ወቅት ያለመታከት ይጮህ የነበረው ወያኔ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ታዲያም፣ አንዳንዶቻችን ኧረ እነዚህ ሰዎች ወዴት፣ ወዴት ያሉ ነው ማለታችን አልቀረም። ከምርጫው መጠናቀቅ ማግስት የምርጭ ቦርድን ሥልጣን በመንጠቅ ኢህ አዴግ ምርጫውን አሸንፎአል የሚል ዜና መለስ ከሰዓት እላፊ ጋር ሲያውጅ ሕዝቡን ለአመጽ መጋበዙ መሆኑ ይታወቅ ነበር። ሕዝቡ ግን ሁኔታውችን በሰከነ አእምሮ እየተከታተለ ቢቀጥልም፣ ሰኔ 1 ቀን 1997 ራሳቸው ቀስቅሰው በመግባት ትልቅ ትንሽ ሳይሉ፣ በሰላም፣ በባዶ እጅ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ መብቴ ነው ብሎ የወጣውን እያሳደዱ ቆሉት። በጥቅምት 1998ም በአብዘኛው የኢትዮጵያ ግዛቶች ያለምንም ማመንታት ትምህርት ቤት ግቢ ድረስ ገብተው

እስከመግደል ደረሱ። ሌላውን ዘረኛ እያሉ እነርሱ ግን ዘር እየመረጡ ገደሉ፣ አቆሰሉ፣ ደበደቡ፣ አሰሩ ሕዝቡ በዘር የማያምን መሆኑን ያሳየውን ፓርቲንም በታተኑት። የሰላማዊ ትግሉንም አደጋ ውስጥ፣ የሰላማዊ እንቅስቃሴውንም አደጋ ውስጥ ጣሉት። የኢትዮጵያ ሕዝብ ዋናው ጥላቻ በወያኔ-ኢህአዴግ የዘረኛ ፖሊስ ላይ እንጂ በትግራይ ሕዝብ ላይ እንዳይደል ይታወቃል። እንዲህ ዓይነት የጅምላ ጥላቻ የለውም። ከማንም በላይ እንዳይንቀሳቀስ በሆዱ የሚሰማውን እንዳይናገር፣ የፈለገውን እንዳይደግፍ ተደርጎ ያለው የትግራይ ሕዝብ እንደሆነ የማያውቅ ቢኖር ኢትዮጵያ ውስጥ ያልነበረ ነው። ወደ ግራና ቀኝ እንዳያይ በወያኔ ካድሬዎች ተከርችሞ ያለ ሕዝብ ነው። ምናልባት ያ ጊዜ ደርሶ ሕዝቡ ከፊት ተደርጎ ቢታይ ምን ጉድ ተሸክሞ እንደነበር ይነግረን ይሆናል፣ ከምንም በላይ ልናዝንላቸው ይሆናል። እነርሱ ግን በአጠቃላይ ሌላው ሕዝብ በትግራይ ሕዝብ ላይ ጅምላ ጥላቻ እንዳለን አድርገው፣ አስመስለው የትግራይን ሕዝብ ይቀሰቅሳሉ። ርሳቸው ኢንተርሐሞይን እየፈጸሙ ወደ ሌላው ለማላከክ ይሞክራሉ። የማይረባ ተስፋቢስ ሙከራ።

እንግዲህ የቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ ታጋይና አባል ነኝ ባዩ ጸሐፊ፣ ከቴዎድሮስ ያስተሰርያል ዜማው የመግቢያውን ስንኝ ቆንጸል አድርጎ በቴዲ ላይ ያለውን ጥላቻ በዘረኝነት ውንጀላ የትግራይን ሕዝብ በአንድ በኩል ለማሳየትና ለማሳመን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአጋጣሚውም በቴዲ ላይ ካራ የሚዘጋጅበት መንገድ ጥርጊያ ለማሳየት እንደሆነ መገመት አዳጋች አይሆንም። በዚህ መጽሐፍ ላይ እንዳይሞቱ እንዳይድኑ ተደርገው ከተሳሉት መካከል ፕሮፌሰር መስፍን፣ አርቲስት ደበበ እሸቱ አንድ ዙር ምታቸውን ተቀብለዋል። ሌሎቹ ዕጣ ፈንታቸውን ይጠብቃሉ። ቴዲ እየቀመሰ ነው። መጽሐፉ በታተመ በዓመቱ ነው ወያኔ ሲቆፍሩለትና ሲጎነጉኑለት ቆይቶ ባዘጋጁት መረባቸው ጠልፈው የጣሉት። እንግዲህ ከዚህ ማየትና መረዳት የምንችለው፣ ወያኔ-ኢህአዴግ እንደአነፍናፊ ውሻ እያደባ ተቃዋሚዎችን፣ ወይም ተጻራሪ አሳብ ያላቸውን እንደሚያሳድድና እንደሚያጠፋ መገንዘብ ያቻላል። ወያኔን ያመነና ጉም የዘገነ አንድ ናቸው ብል አንስማም? ትላላችሁ።

ታዲያ ወገኖቼ የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶችና ፍትህ ከመቼውም ይበልጥ ወደ መቃብር እየወረደበት የሄደበት ጊዜ ነው። ይህን ስል ግን ዳኛና ዳኝነቱን ሳይሆን፣ የዳኝነቱን አስተዳደር፣ የፍትሁን አስተዳደር ማለቴ ነው። ከዚህ በፊት ለመጠቆም እንደሞከርሁት፣ በተለይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ፣ በከፍተኛም ሆነ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጠንካራ ዳኞች እንዳሉ አውቃለሁ። ከፖለቲካ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ሲቀርቡ ወደ እነዚህ ዳኞች ዘንድ እንዳይመሩ ይደረጋል። በፍ/ቤቱ እንደዚህ ዓይነት ጉዳዮች የሚመሩት በመንበረፀሐይ ታደሰ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ም/ፕሬዚዳንት፣ እና ደሳለኝ በርሄ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት በታማኝነታቸው ወደ ተመረጡ ዳኞች ነው። እነርሱ ካላመኑበት አንድ ዳኛ ምንም ቢሰራ ካለበት ፈቀቅ አይልም። የእንጀራ ልጅ ሆኖ ይቀራታል እንጂ። ብዙ ጠንካራ ዳኞች ፍ/ቤቶችን ለቀው የሚወጡትም በዚህ ምክንያት ነው። እነዚህ የፍ/ቤቶቹ ኃላፊዎች በመለስ ሳይታዘዙ የሚታዘዙ፣ ሳይነግራቸው የሚናገሩ፣ መለስን ከእግዚአብሔር በላይ የሚያመልኩ፣ የመለስን የልብ ትርታ ለማንበብ ሌት ተቀን ደፋ ቀና የሚሉ ናቸው። እናም፣ ለፍ/ቤቱ መሞት፣ በበአምባገነኑ አስተዳደር ሥር ለመውደቅ በዋናነት ተጠያቂዎቹ እነዚህ ሁለቱ ናቸው ለማለት ያስደፍረኛል።

በተለይም፣ ከምርጫ 97 ማግሥት ወያኔ የወሰደውን እኩይ ርምጃ ለማሳካት አዲስ ችሎት በተመረጡ ዳኞች ተቋቁሞ ውጤቱ ታይቶአል። አሁን ደግሞ ወያኔ እየወረደ ወደ ግለሰብ ላይ ደርሶ ወጣቱን በዚህ በጠቆምሁት መጽሐፍ ላይ እንዳሰፈሩት መልክ አጥምደው በእስር ሕሊናውንና አንደበቱን ሊሸብቡት እይሞከሩ ነው። ጉዳዩን የያዘው

በዚህ በኩል የታወቀው ዳኛ ነው። በእጅጉ ሊታመን በማይችል ሁኔታ ሕሊናውን በሸጠ መልክ ቴዲ እንዲከላከል በይኖበታል። ለመስከረም 27 ቀን 2001 እንደተቀጠረም እናውቃለን። የበላ ዳኛ የወጋ መገኛ ዓይነት አውቆ የተኛ ዳኛ ፊት ምኑ እንደሚፈርስ ግራ ይገበኛል እንጂ፣ ቢኖር እንኳ እንዴት እንደሚቻል አይገባኝም።

አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ፤ ጥንት በዚያን እሰጥ-አገባ ወቅት ነው፤ ዳኝነት በዋርካ ሥር በሚያስችሉበት ወቅት፣ የከሳሽና የተከሳሽ እግር በገመድ ታስሮ፣ ከሳሽ ፊትለፊት ተከሳሽ ከኋላ ሆኖ ወደ ችሎቱ በሚካሄድበት ወቅት፣ በዚያ ደጉ ዘመን፣ ትግራይ አከባቢ ነው አንድ ከሳሽና ተከሳሽ ወደ ችሎቱ ቀረቡ። ይህን ያህል እሰጥ አለ ለዳኝነቱ ከሳሽ፤ ተከሳሽም ይህን ያህል እኔም አገባ አለ። ክርክራቸውን ጀመሩ። ከሳሽ ጉዳዩን አቀረበ። ተከሳሽም በተራው መከላከያውን መናገር ጀመረ። ዳኛው ግን ዝምበል ቀጣፊ፣ እብለተኛ፣ ሸረኛ....እና የመሳሰሉትን ማስፈራራዎችን ሲወርድበት፣ ተከሳሽ ይህን ጊዜ ሁሉም ነገር ገባውና መላ መጣለት። የነበሩበት ችሎት ጫካ ውስጥ ባለ ዋርካ ሥር ስለነበር ወደ ቁጥቋጠው የሌባ ጣቱን ቀስሮ ኧረ ጌቶች! ኧረ ጌቶች! ....! እያለ መጮህ ጀመረ። ዳኛው ተከሳሹ ወደ ሚይሳይበት ዞር፣ ከሳሽም ዞር ብለው ምንድነው? ምንድነው? እያሉ ተደናገጡ። ይህን ጊዜ አጅሬ ተከሳሽ ጊዜም አልወሰደ እግሬ አውጭኝ ብሎ እልም አለ። እናም፣ በኋላ ተይዞ ሲጠየቅ እንደ ምን ላድርግ ዳኛው የኔን መከላከያ ከመስማት ይልቅ የስድብ ናዳ፣ መስፈርራቶችን ያወርዱብኝ ጀመሩ። በቃ ፍትህ እንደማላገኝ ገባኝ። “የበላ ዳኛ የወጋ መገኛ” አንድ ናቸው ብሎ እርፍ አለ ይባላል።

እናም፣ ለመከላከል መጀመሪያ በተከሳሹ ላይ ሊመሰከርበት ይገባልማስረጃ ከሕጉ ጋር ሲገናዘብ። በቴዲ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች አንዳቸውም እንደክሱ አላስረዱም፤ እናም፣ አልተመሰከረበትም። ክሱ የቅንብር፣ ዳኝነቱም የቅንብርሆነና ቴዲ እንዲከላከል ተበይኖበታል። ቴዲ ምኑን ሊከላከልና ሊያፈርስ ማስረጃ እንደሚያቀርብ አይገባኝም። ለነገሩ መቼም ደንብ ነውና ላቅርብ ካለ፣ ቴዲ ሊያቀርብ የሚችለው ማስረጃ፣ ወንጀሉን ፈጽሞአል በተባለበት ዕለትና ሰዓት የነበረበትን ቦታ የሚያስረዳ ነው። ቴዲ በእንዲህ ማስረዳቱ የሚከብደው አይመስለኝም። ዳር ምን ይሆናል ዳኛ ልዑል ግን፣ አይኑን ጨፍኖ የቴዲን ማስረጃ የተጠና ነው፤ የዐቃቤ ሕግን ማስረጃ አላስተባበለም ብሎ መወሰኑ አይቀርምና።

በሌላ በኩል ግን ሳልል የማላፈው፣ ገና የቴዲ ጉዳይ እንደተጀመረ፣ ስዊድን ራዲዮ እንደገለጽሁት ከሁሉም የገረመኝ ቴዲ ጠበቃ ሚሊዮን አሰፋን ለጉዳዩ መቅጠሩ ነው። ቀደም ብሎ ሚሊዮን አሰፋ እስከ ግንቦት 1988 ዓ.ም(እ.ኢ..አ) ድረስ የማዕከላዊ በሚባለው ፍ/ቤት የከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኛ የነበረ፣ በ1988 ፌዴራል ፍ/ቤቶች ሲቋቋሙ ተቀንሶ ጠበቃ የሆነ ነው። በምርጫ 97 ማግሥት በመንግሥት ሚዲያዎች፣ በተለይም በቴሌቪዥን ላይ እየወጣ አብሾ የጠጣ ይመስል በቅንጅት ፓርቲና በመሪዎቹ ላይ የሚሰነዝረው ሕግ ሳይሆን ተራ የነቀፋ ዱላ የሕግ ሰው መሆንን እስከሚያስጠላን ድረስ አገሽግሾን እንደነበር ትዝ ይለኛል። ቴዲን ምናልባትም መካሪዎቹ የመንግሥት ወገን ነው በሚል አሳምነው ይሆን አላውቅም ጠበቃው ሆኖ ስሰማ አስደንግጦኛል። ነገሩ ውሻ እበላበት ይጮሃል እንዳይሆን ፍርሃቴ ከጅምሩ ነበር። እናም፣ እንዴት እንደተከራከረ አላውቅም። አሁን፣ ፍ/ቤቱን ተዳፍሮአል ተብሎ ወደ ቴዲ ተወርውሮ የወጣበትም ሁኔታ አላማረኝም። ምን ብሎት እንደወጣ አይታወቅምና። ወያኔ የማይሰራው ነገር የለምና።

ግና፣ ምንምን ይሁን ምንም ወጣቱ የፖፕ ሙዚቀኛው ቴዎድሮስ ካሳ በአንዲት አገር በኢትዮጵያዊ በሁሉም ልብ ውስጥ ገብቶአል። ማንም ምንም እንዳያደርገው በፍቅር ታጥሮአል። እነርሱ ይብላኝላቸው እንጂ፣ መሰላቸው እንጂ፣ የቴዲ ልብ ፈርጥሞአል።

ጀግናነው። ሁሉም በያለበት ዓላማውን ይከተሉ ዘንድ ፋና ወጊ ሆኖአል። ወያኔ ቴዲን ምንም አላደረገውም ጀግንነቱን አበሰረለት እንጂ፤ አጸደቀለት እንጂ። ከኢትዮጵያን አልፎ ተርፎ ስሙ እንዳንድ አገር ወዳድ፣ እንደአንድ ገናን ፖለቲከኛ በታወቁ የውጭ ሰዎች እየተናኘ ነው። በቃ የቴዲ እናት የጎበዝ እናት ናት። የጀግና እናት ናት። ሐዘን አይገባትም፣ ኩራት እንጂ። እናም፣ ያ ጊዜ መምጣቱ አይቀርምና ቴዲ ልብህ ይደንደን፣ ሕሊናህም ይጠንክር፣ አይዞህ! መልካም ስም ከእንቁ በላይ ነውና።

** በሰኔው እና በታህሳስ 1997 በንጹሃን ዜጎች ላይ ወያኔ የፈፀመውን ግፍ እንዲያጣሩ ከተሰየሙት አንዱ ናቸው ዳኛ ወልደሚካኤል መሸሻ። መለስ ዜናዊ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ውሳኔ እንዲያስተላልፉ ከተነገራቸው በሁዋላ ይህንን ከማደርግ ስደትን እመረጣለሁ በማለት ሞያቸውን፡ ሃብት-ንብረታቸውንና የሚወዱዋት ሃገራቸውን ጥለው በመሰደድ አሁን ከቤተሰቦቻቸው ጋር በኔዘርላንድ ይኖራሉ።*